# ጦርነቱ ተጀምሯል፤ አሸናፊውም በቅርብ ይለያል!

**ይሄይስ አእምሮ**

**June 16, 2016**

አንድ ጊዜ በድብቅ ሌላ ጊዜ በግልጽ ለበርካታ ዓመታት ሲካሄድ የነበረው ጦርነት አሁን ለይቶለት ፈንድቷል፡፡ ብዞዎቻችን ስንጠብቀው የነበረ በመሆኑ አላስደነቀንም፤ እንዲያውም በጣም ዘግይቶ በመጀመሩ ምክንያት ሳንገረም የማንቀር ሰዎች እንደምንኖር እገምታለሁ፡፡ ኢሣይያስ ሣይቀር የዚህን የጦርነቱን መጀመርና የመጨረሻ ዕጣ ፋንታ በሚመለከት በትንቢት መልክ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር፤ የሰማውና ከቁብ የቆጠረው ግን አልነበረም፡፡ ይሄውና አሁን ግን ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ግድ ሆነና በአራቱም ድንበሮች ማለትም አቅጣጫዎች ውጊያው ተጀምሮ እየተጧጧፈ ይገኛል፡፡

የእግዚአብሔር ቀን ቀርቧልና አልቅሱ … እጅ ሁሉ ትዝላለች፤ የሰውም ሁሉ ልብ ይቀልጣል፡፡ ይደነግጣሉ፤ ምጥና ሕማም ይይዛቸዋል፤ እንደምትወልድ ሴትም ያምጣሉ … እነሆ ምድሪቱን ባድማ ሊያደርግ ፣ ኃጢአተኞችዋንም ከእርሷ ሊያጠፋ ጨካኝ ሆኖ በመዓትና በጽኑ ቁጣ ተሞልቶ የእግዚአብሔር ቀን ይመጣል፡፡ … ዓለሙን ስለክፋታቸው፣ክፉዎቹንም ስለበደላቸው እቀጣለሁ፤ የትዕቢተኞችንም ኩራት እሽራለሁ፤ የጨካኞቹንም ኩራት አዋርዳለሁ፡፡… ትንቢተ ኢሣይያስ 13፤ 6-16

የትኛው ጦርነት እንደተጀመረ አሁን ግልጽ ማድረግ አለብኝ፡፡ የተጀመረውና ተፋፍሞ በመቀጠል ላይ የሚገኘው ጦርነት አንባቢዎች እንደምትገምቱት የኢትዮጵያና የኤርትራ ሣይሆን በሰው ልጆችና በክፋት ሥራቸው መካከል ለዘመናት ሲግልና ሲቀዘቅዝ የመጣው የፍጻሜው ጦርነት ነው፡፡ የተለያዩ ስያሜዎችን መስጠት ይቻል ይሆናል፡- አርማጌዶን፣ ምፅዓት፣ የዓለም ፍጻሜ ወዘተ.፡፡ በየትኛውም ስሙ ጥሩት – የመጨረሻው መጨረሻ ግን በየበራችን ቆሞ እያንኳኳ ነው፡፡

በነገራችን ላይ ባለፈው ሰሞን ስለ አበበ ተ/ሃይማኖት የጻፍኩትን መጣጥፍ በሚመለከት አንዳንድ አስተያየቶች በግል የኢሜል ሣጥኔም በድረ ገፅም ሣነብ የተሰማኝ ነገር አለ፡፡ ያም በተለይ የተቃወሙኝን በተመለከተ አንዳንዶቻችን ከእውነቱ ምን ያህል እንዳፈነገጥን የተገነዘብኩበት መራራ እውነት ነው፡፡ ጥቂት ድረ ገፆች እውነት እንደጦር እየወጋቻቸው ሣይሆን አይቀርም ስንት የደከምኩበትን ጽሑፌን የቅርጫት እራት አድርገው አስቀርተውብኛል፤ ትዝብት ይውረሱ፡፡ ይሄ ዘር የሚሉት ጣጣ ሲጠፋና (በቅርብ የሚጠፋ ከሆነ) ከዚያ ጠባብ ማዕቀፍ (shell) ሲወጡ አሁን ምን እየሠሩ እንደሆነ በማስታወስ ራሳቸውን ሊወቅሱ እንደሚችሉ እገምታለሁ፡፡ በተረፈ በዚያ ጽሑፍ ያልኩት ሁሉ መዛነፍ የሌለበት ጥሬ ሃቅ ነው፡፡ ልጨምርልህ ከፈለግህ አሁንም፡፡

ትናንት ማታ አንድ ሰው ጋ ስንጫወት ይሄው የዘር በሽታ ተነሣና እንዲህ አለኝ፡፡ "እንዴ፣ ምን ማለትህ ነው ይሄይስ! የነዚህ ሰዎች ዘረኝነት እኮ ድንበር ብሎ ነገር አያውቅም፡፡ ለገሀር አካባቢ አንድ የአሸዋና ስሚንቶ መሸጫ ነበረ – ታስታውሰዋለህ? አሁን ትልቅ ፎቅ ተሠርቶበታል፤ ከሥሩም የነዳጅ ማደያ ተመርቆለታል፡፡ የዚያ ቦታ ባለቤት ምን እንደሆነ ሰምተሃል? … ለነገሩ ስንቱን ጉድ ልትሰማ ትችላለህና፡፡ እናልህ ያ የቀድሞውን ባለቤት አንድ ትግሬ ቀምቶት ባዶ ሙልጩን ሰደደውና ሰውዬው በንዴት ራሱን ሰቅሎ ሞተ፤ ቤተሰቡም ተበተነ፡፡ ትግሬው አሁን እየተንጎማለለ ባለብዙ ሀብት፣ ባለብዙ ሚሊዮኖች ብር ሆኖልሃል፡፡

እንዲህ ያለ የጠነባ የዘረኝነት ግፍ አገር ምድሩን ሞልቶት ትግሬ ሲንቀባረር ሌላው አንገቱን ደፍቶ ሲዋትት ይኖራል ወንድሜ – መኖር ተብሎ፡፡ በዚህ መልክ ሀብት ንብረቱን፣ የሞቀ ትዳሩን፣ የማትተካ ሕይወቱን፣ ገንዘቡን ያጣው ዜጋ ቁጥር ሥፍር የለውም፤ ራሱን የገደለው ዜጋም እጅግ ብዙ ነው፤ ማርካቶን ከጉራጌ ያጸዱት እንዴት አድርገው እንደሆነ መቼም ሳትሰማ አትቀርም – ይሄውልህ – አንድን ነጋዴ ውጣ አይሉትም – እንዲወጣ ግን ያደርጉታል፤ ኪራዩን ሰማይ ይሰቅሉና፣ ግብሩን ሰማይ ይሰቅሉና፣ የዕቃ ቀረጡን ሰማይ ይሰቅሉና ምድረ ጉራጌና ሌላዋ ዜጋ በብስጭት የመርዝ "ዊስኪዋን" እያንደቀደቀች ስትሞትላቸው ወይም በእግር አውጪኝ ለስደት የመከራ ሕይወት ከሀገር ስትወጣላቸው ዌም ጨርቋን ጥላ ስታብድላቸው … እነሱ ያኔ በቆረጣ

ሰዎቻቸውን ያስቀምጡበታል – ካላንዳች ግብር፣ ካላንዳች ቀረጥና ለስም በምትሆን ጥንጥዬ ኪራይ።

ደስ ካላቸው ይቀሙህና አንተ በነሱው ፍርድ ቤት ስትንከራተት ትኖራለህ – በመጨረሻም በዘራቸውና በፖለቲካቸው ገብተው ያስፈርዱብሃል ፐ! እሱማ ቀላል ነው፤ ባንተ ላይ ማስፈረድ? በስማም፤ በተለይ ዐማራ ከሆንክማ የቆቅ ሥጋ ነህ – የምትጣፍጣቸው ግሩም ጣዕም ያለህ ፍጡር። ፈጣሪን ረስተው አንድያውን ለሰይጣን ስላደሩ ለማንም ሕይወት መንከራከስና የትም ወድቆ መቅረት ቅንጣት ታህል አያዝኑም። ትናንት ደግሞ አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሄጄ አንድ ጓደኛየ በክበባቸው ምሣ ሲጋብዘኝ የታዘብኩት ነገር በጣም የሚገርም ነው።

የክበቡ ሠራተኞች በሙሉ፣ የክበቡ ተጠቃሚዎች በትንሽ ግምት 90 በመቶ የሚሆነው፣ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ከሞላ ጎደል ሁሉም ትግሬዎች ናቸው። ነገሩ የመከላከያ መሥሪያ ቤት በመሆኑ ሁሉም እነሱ ቢሆኑ አይፈረድም። ኧረ አለልህ እንጂ ማዘጋጃ ወይ ሌላ ተራ መሥሪያ ቤት … የትም ሂድ ብሔራዊ ቋንቋው ትግርኛ የሆነ ያህል እስኪሰማህ ድረስ እነሱ ናቸው ሠራተኞቹም ሆኑ አዛዥ ናዛዦቹ። ለዚህ ሳይሆን እኮ አይቀርም የጀርመን ኤምባሲ ትግርኛ የማይችል ሰው አልቀጥርም እስከማለት የደረሰው – ያው እነሱስ ዘረኛ አይደሉ? ባለጌዎች። የሚገርም ትንግርት ነው እየታዬ ያለው፣ ይህን ቅጥ ያጣ አሠራር ማንና እንዴት እንደሚያስተካክለው ቆይቶ ማየት የሚችል ሰው ታድሏል ልጄ።

እኔ በበኩሌ እስከዚህ ዐይናቸውና ሁለመናቸው የታወረ አይመስለኝም ነበር። ለይቶላቸዋልና እባክህን…” ሰውዬውን አስቆምኩት። በአሁኑ ሁኔታችን አንድ ሰው ብሶት መናገር ከጀመረ ማቆሚያ የለውም። እንደዶፍ ዝናብ ያዥጎደጉደዋል። ይሄ እንግዲህ ከማሰር መግደላቸው፣ በፍትህ ስም ግፍና በደል እየሠሩ ንጹሓንን ከማሰቃየታቸው፣ ሕዝብን በአስተዳድራና በኑሮ ውድነት ከማንላታታቸው፣ ብዙኃንን ለስደት ከመዳረጋቸው፣ ዐይን ዐይን የከተማዋን ቦታዎች ለንግድም ሆነ ለመኖሪያ ለነሱ አባላት (ብቻ) ከመስጠታቸው … በተጨማሪ በኢኮኖሚውና በሀገራዊ ጥቅም ላይ የሚሠሩት የማንአለብኝነት በደል ነው። ይህን ስንናገር አላትምም የሚል ቢኖር የነሱን ዕጣ ይካፈል፤ እንደነሱ መጨረሻው የእቶን እሳት ይሁን።

አዎ፣ ይህን ግፍ መደበቅ ወይ ለመደበቅ መሞከር የግፉ ባለቤት የመሆን ያህል ነው። ወንድምህ ሰው ግደሎ አንተ ቤት ቢደበቅና ከሕግ ቢሠወር አንተም ከሱ ባልተናነሰ ወንጀለኛና አጥፊ ነህ። የሰማይና የምድር ሕግጋትና ሕገ ልቦና ተባብረው ፍትህን መታደግ ካልቻሉ ሰዎች ከዕቃነት አልተለዩምና ሰው አይባሉም። የወንድሙን ጥፋት የሚሸፋፍን የወንድሙን የበደል ዕጣ ይጋራ፤ በቃ።

ለምን ወደ ተጀመረው ጦርነት አንሄድም?

እንጦስ ስለተባለ የወያኔ ጳጳስ ኢካድፍ ድረገፅ ላይ አንድ አስገራሚ ሀተታ ሰሞኑን አንብቤያለሁ። በአሜሪካን ሀገር በዚሁ ሰሞን በአንድ ግለሰብ የተፈጸመው የጅምላ ግድያም ገና ትኩስ ዜና ነው። መነሻየ እነዚህ ሆነው መድረሻየ ግን እንደምከንያት ሆኜ በትንሹ የአንድ ሰው ነፍስ መዳን ነው፤ “እሳት ተነስቷልና ራሳችሁን አድኑ፤ ሀብት ንብረታችሁንም አሽሹ” ብሎ መጮኽ ነውር የለበትም። የማይቀለበሰው ጦርነት ተጀምሯልና ተገቢውን ጥንቃቄ እናድርግ ማለት ጤናማ ነኝ ብሎ ከሚያስብ ዜጋ የማይጠበቅ እንዳልሆነ በመገንዘብ ቀጣዩን ሀተታ በጥሞና እንመልከት።

ስለዓለም ፍጻሜ የተጻፉና የተነገሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊም (ሃይማኖታዊ)ም ይሁኑ ሰብአዊ ትንቢቶች እጅግ ብዙ ናቸው። የድረገጽ ዳሰሳ ብናደርግ በሺዎች የሚቆጠሩ ንግርቶችንና መላ ምታዊ ግምቶችን በሴከንዶች ውስጥ እናገኛለን። አሁን “እከሌ ምን አለ” ወይም “ያ መጽሐፍ እንደዚህ አለ” የሚለው አካሄድ ጊዜ ያለፈበት ስለሚመስለኝ በምናያቸው አስቀያሚ ግን የሚጠበቁ እውነቶች ላይ ብቻ በመመርኮዝ የዘመናችንን ፍጻሜና የጦርነቱን መፋፋም ለቅጽበት ያህል እናስታውስ።

በፍሎሪዳ ግዛት ሰሞኑን በሶዶማውያን የምሽት ክበብ ውስጥ የተፈጸመው የጅምላ ግድያ ውጤቱ አሣዛኝ ቢሆንም ምክንያቱ ግን ተገቢና የፈጣሪ መቅሰፍት ነው የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ የኖኅን የውኃ ጥፋትና የሎጥን የድኝ እሳት ዝናብ በሚያስታውሰን በዚህ ፍጅት ወደ ሃምሣ የሚጠጋ ሰው ሲገደል 53 አካባቢ ቆስሎበታል – ከነዚህም ስድስቶቹ በጽኑ የተጎዱ፡፡ ይህ አደጋ ያላሳዘናቸው ሰዎች ሞልተዋል፤ ያሳዘናቸውም እንዲሁ ብዙ ናቸው፡፡

ያላዘኑት ሰዎች ምክንያታቸው ሚኞቹ ዱሮውን በቁም ሞተዋል ከሚል ሃይማኖታዊ መነሻ ነው – ይህ እሳቤ ምናልባት የንስሃ ጊዜን ያለማሰብ ችግር ይኖርበት ይሆናል፡፡ በተረፈ ለሰይጣናዊ ድርጊትና እርሱን ተከትሎ ለተፈጠረ ቅጣት አቦካቶ ሆኖ መገኘት አጠያያቂ ይመስላል፡፡ እግዜር የፈቀደው ሆነ፤ የተገዳደሉት ደግሞ ጎልያድና ጎልያድ እንጂ ዳዊት በዚህ ትዕይንት የለበትም፡፡ ማለቴ ገዳዩም የዚያ ሥፍራ አዘውታሪና አባልም የነበረ መሆኑ በቀድሞ ባለቤቱ ተመስክሯል፤ ስለዚህ “አህያ ለአህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም” ነው፡፡

ወጣም ወረደ ይህ ክስተት የተጀመረው የታላቁ ጦርነት አካል ነው፡፡ የዓለም ሕዝብ በአሁኑ ወቅት እየተነዳ ያለው በዲያሎብስ መሆኑ ፀሐይ የሞቀው እውነት ነው – ሀፍረትን ለናቀው ድፍረቴ ግን ይቅርታ፡፡ እናም የታላቁ መሪያችን የሣጥናኤል ዘመን እየተገባደደ በመሆኑ ዐይኑን በጨው አጥቦ የዓለምን ዜጎች ወደግዛቱ ለማስገባት በተለይ ባለፉት 2000 ዓመታት የማያደርገው ጥረት አልነበረም፡፡ የተሳካለት ብዙ ነገር አለ፤ ያልተሳካለትም አለ፤ ዝርዝሩ ብዙ ነው፡፡

ከተሳካለት ውስጥ ጥቂቶቹን ማየት እንችላለን፡፡ ሰይጣን 500 ባልሞሉ ጥቂት ዓመታት ውስጥ ዓለምን መቆጣጠር የምትችል ታላቅ ኃያል ሀገር ፈጥሯል፡፡ ይህ በራሱ ትልቅ ስኬት ነው፡፡ ይህችን ሀገር የሚመሩ ጎቡኣኑ የዐውሬው ታዛዦች በአንዲት ሀገር ውስጥ ሁለት መንግሥታትን በማቆም ያሻቸውን እየሠሩና የዓለምን ሀገራት መሪዎች እንደፈለጉ እያሽከረከሩ ናቸው፡፡ በአንድ በኩል ዴሞክራሲ በጠራራ ፀሐይ የሚረሸንበትን ኢትዮጵያን የመሰለች ሀገር መሪዎች ሲሸልሙና ሲያሞግሱ ቢገኙ ወይም የዴምክራሲ ቃል ከናካቴው የማይጠራባቸውንና በተለይ የሴቶችን መብት የሚገፉ እንደሳዑዲ ያሉ ሀገራትን አቅፈውና ደግፈው ቢገኙ ለነሱ ምንም ማለት አይደለም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝብ የሚወዳቸው መሪዎች ያሉባቸውንና በአንጻራዊ አነጋገር የተሻለ ዴሞክራሲያዊ አካሄድ የሚከተሉ ሀገራት መሪዎችን በሣተና ሰላዮቻቸው ቢያፍኑና ቢያስገድሉ ከማጉተምተም በስተቀር ወቃሽና ዳኛ የለባቸውም፡፡ አንዱ መንግሥት በግልጽ የሚታይና በዴሞክራሲ ጭምብል የዓለምን የኃይልና የፖለቲካ ሚዛን እንደፈለገው የሚያደርግ ነው፤ ሌላኛው ከ 300 በማይበልጡና በማያንሱ ሥውር የቃል ኪዳን አባላቱ ዋናውን መንግሥት ከመጋረጃ በስተጀርባ ሆኖ በጥብቅ እየተቆጣጠረ የአባታቸውን የሣጥናኤልን ዓለምን ወደ አሃዳዊ የጨለማ ግዛት ለውጦ የመግዛት ህልም እውን ለማድረግ የሚጥር ነው፡፡ ይህ እውነት በሚዲያ እንዳይወጣ ከፍተኛ አፈናና ቁጥጥር ቢደረግም የፈለገ ግን አያጣውም፤ እኛ እዚህ ግቡ የማንባለው ውዳቂ ዜጎች እንኳን አላጣነውም፡፡

ቀደም ሲል በአዩኝ አላዩኝና እንደማፈርም እያሉ ህልማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ይሞክሩ ነበር፡፡ አሁን አሁን ግን ድፍረታቸውና ዕብሪታቸው ወሰን አጥቶ መጣና ሌላው ቀርቶ ግብረ ሶዶማዊ “የዓለም መሪ” እስከመሾም በመድረስ “ምን ታመጣላችሁ?” እያሉን ነው፡፡ እኛማ ምን እናመጣለን ለነገሩ፡፡ ግን የሁሉም ሥልጣኔዎችና የሁሉም ድፍረቶች መጨረሻ ምን እንደሆነ ስለሚታወቅ ይህ ትዕቢታቸው የት ድረስ እንደሚወስዳቸው በጣም በቅርብ የምናየው ይሆናል፡፡

ሰይጣን ሰውን የሚያረክስበት ብዙ መንገድ አለው፡፡ ትልቁ ግን ፀረ-ተፈጥሮ ማድረግ ነው፡፡ ይህን ታዲያ ልብ እንበል፤ ከዚህ ትልቅ ፀረ-ተፈጥሮ ድርጊትም ራሳችንን እናርቅ፡፡ በዚህ ሰፊ ጎዳና ውስጥ የምንገኝ ሰዎች ካለን አሁኑኑ እንንቃና በአፋጣኝ እንመለስ፤ ይህ ነው የኔ መልእክት፡፡ ይህ ነው የኔና መሰሎቼ ወንድማዊ ጥሪ፡፡ “መብቴ ነው፤ ምርጫየ ነው፤ ምንም

ማድረግ አልችልም – የተፈጥሮ ዝንባሌየ ነው …” ቅብጥርሶ ብንል አያዋጣም፡፡

… ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኩስነት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው፤ … ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም ለባህርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስህተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ፡፡

… እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤… ሮሜ 1፤ 24 – 28

መጽሐፍ አልጠቅስም ብዬ ነበርና ይቅርታ፤ ግድ ሆኖብኝ ነው፡፡ እናስ እንግዲህ ምንድነው የምንጠብቀው? የባለአንድዐይናውያኑ ዋና ተወካይ በሥርዓታቸው መሠረት ዕድገቱን አልፎ በግልጽ የሶዶማዊነት መንፈስ ዓለምን እየዞረ ስለነሱ መብት ሲከራከርና መብታቸውን ያልጠበቀ ሀገር ላይ ማዕቀብ እስከመጣል ወይም የተጣለን ማዕቀብ እስካለማንሣት ሲደርስ የኛን በመሰሉ ምሥኪንና ድሃ ሀገራት የሚገኙ የነሱው ተወካይ ቡችላ አጋንንት የሚገዙትን ሕዝብ በቁሙ እንጦርጦስ ሲከቱት ምን አሉ? አበረታቷቸው ወይንስ ተቆጧቸው? እውነቱ ይህ ነው – ገዢዎቻችን የነሰው ሎሌዎችና በምግባርም በጠባይምም የሚመሳሰሏቸው የሣጥናኤል ጭፍሮች ናቸው፡፡

እንደነሱ አለመሆን ታዲያ በምድር ቢቀር በሰማይ ማለትም በቀጣዩ ሕይወት ዋጋ አለው፡፡ ይህን ልብ እንበል!! ሶዶማውያን ዓለምን እያበሻቀጧት ነው – ጥምብ እርኩሷን እያወጧት፡፡ ያቺ የትንቢት መፈጸሚያ ኃያል አገር እስካሁን ወደ 11 የሚደርሱ መሪዎቿ በዚህ ነገር እንደሚታሙ መዛግብት ይናገራሉ – በነገራችን ላይ ይህ ነገር ለነሱ ምንም ነውር የለበትም – ምክንያቱም አባታቸው እንዲሆኑለትና እንዲያስፈጽሙለት የሚያዛቸው ዋና ምሱ ነውና፡፡ ሰውን ማሳት በተለይ ትልልቅ የሚባሉትን ከመስመር ማስወጣት የዲያብስ ዋና መገለጫው ነው፡፡ አንድን ጳጳስ ማሳት አንድ ሺ ምዕመናንን ከማሳት ይበልጣል፡፡ ለምን ቢባል ጳጳሱን ፍየል እያየ የሚጠፋው በግ በብዙ መቶ ሺዎች ይቆጠራልና፡፡ የተያያዝነው ጦርነት እኮ በጣም ከባድና ሰው ያላወቀልን ነው ጎበዝ! ሆ!

ወደነኞች ስንመጣም እውነቱ ያው ነው – ሊያውስ ባይበስ አይደል? አንድ ወቅት እኔ በኃላፊነት እመራው በነበረ አንድ የግል ጋዜጣ ውስጥ ይሠራ የነበረ ጋዜጠኛ የዱሮው ከርቸሌ ይታሰራል፡፡ ሲፈታ አንድ ግምኛ ጨዋታ ነገረኝ፡፡ ሁለት ካህናት እርሱ በታሰረበት ክልል ታስረው ነበር፡፡ የታሰሩበትን ምክንያት ሲነግረኝ የአሁኑን አያድርገውና በጊዜው በጣም ደነገጥኩ – አሁንማ እንኳን ቀሲስ ምድረ ባህታዊ፣ ጳጳስና ኤጲስ ቆጶስ ሁላ የተሰማራበት ቢያንስ ደግሞ በመደበኛው በኩል ያልሰነፈበት ተግባር ነው – ስንቱን ስናውቅ? እነዚያ ቄሶች የታሰሩት በግልጽ አማርኛ ሲሳረሩ እጅ ከፍንጅ ተይዘው ነበር – ግብረሶዶማውያን ነበሩ እያልኳችሁ ነው፡፡ መተፋፈር ዱሮ ቀረ ወንድሜ፡፡

ስለዚህ – የነአባ እንጦስማ ሚስት ማግባት ቀላል ነው፡፡ አባ ገብረ ሚካኤል የሚባሉ አሁን በማዕረገ ጵጵስና አቡነ እስጢፋኖስ የሚሰኙ እጅግ የተከበሩ ወያኔ ደግሞ አሥሬ እያገቡ የሚፈቱ መሆቸውን በቅርብ የሚያውቃቸው ሰው ነግሮኛል – ኃጢያቱ በኔ ይሁን ብያለሁ፤ እናንተ ባይሆን “አበስ(ኩ) ገበርኩ” እያላችሁ ሣር ቢጤ ባፋችሁ ያዙልኝ፡፡ አንድም ጳጳስ ከዚህ ውስልትና ነጻ የሚሆን ካለ በበኩሌ ይደንቀኛል፡፡ ከሚቹ ዱርዬ ፓትርያርክ ከጳውሎስ አንስቶ ሁሉም የሲኖዶስ አባል – ጃንደረባ(ስልብ) ካልሆኑ በስተቀር – ሴቱን እንደሸሚዝ ነው የሚለዋውጡት ይባልላቸዋል፡፡ የሰው ሚስት ሳይቀር እያፋቱ

እንደሚያስቀምጡ የታወቀ ነገር እኮ ነው – ያን ታዋቂ አርቲስት ማነው ባልቴት ሚስቱን ቀምቶ ባዶ ያስቀረው? ነውራቸው ተነግሮ ያልቃል እንዴ? እኔ በአንዲት ሚስት ከ 30 ዓመታት በላይ ታስሬ ስኖር – በአንድ እጅ ጣት ከምትቆጠር የጥቂት ጊዜ ውስልትና ውጪ (ሸፋፋም ቢሆን ምክንያት ነበራት) – እነሱ ግን ቀዩዋን ከጠይሟ፣ ወጣቷን ቃ ካለችዋ እያማረጡ … የቀናሁ አስመሰለብኝ ይሆን እንዴ ይሄ ነገር?… ብቻ ይህን ሁሉ ጉድ መጽሐፉ አስቀድሞ ተናግሮታልና አዲስ ነገር የለም፡፡ የሚያሳዝነው ግን የእግዚአብሔርን መንገድ የሚከተል አንድም እረኛ ጠፍቶ ቤተ እግዚአብሔር የሰይጣን መናኸሪያና እንደልብ መፈንጫ መሆኗ ነው፡፡ በነዚህ አለሌዎች የምትመራ ቤተ አምልኮ ወደ ጥፋት እንጂ ወደጽድቅ መንገድ እንደማታስገባ ግልጽ ነው፡፡ እንዲያውም እስካሁን ድረስ ለይቶላት አለመጥፋቷና ምዕመናን አስልመውና ጴንጠው አለማለቃቸው ይገርመኛል፡፡ ሰው ሲጨነቅ እኮ የሚያደርገውን አያውቅም፡፡ አንዳንድ ሞኝ ሰው ራሱን አንቆ የሚገድለው ወይም መርዝ ጠጥቶ ከዚህች ቆሻሻ ዓለም የሚሰናበተው ወዶ አይደለም፡፡…

በነገራችን ላይ ጳጳሣትና መነኮሳት እግዚአብሔርን እያታለሉ በሰዎች ፊት እንዲህ ከሚዋዱ የመጽፉን ቃል ሰምተው እያገቡ ቢኖሩ ይሻላቸው ነበር – በዚያም ከረጉና በአንዲት ሴት ብቻ ከተወሰኑ፡፡ ጳውሎስ የተናገረው ለሚችሉ እንጂ የሥጋ ፍላታቸውን መቆጣጠር ለሚያቅታቸው ዌም ፈጽሞ ለማይቻላቸው አስመሳዮች አይደለም፡፡

… ሰው ሁሉ እንደኔ ቢሆን እወዳለሁና፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የፀጋ ስጦታ አለው፤ አንዱ እንደዚህ፣ ሁለተኛውም እንደዚያ፡፡… ላላገቡና ለመበለቶች ግን እላለሁ – እንደኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው (በድንግልና እና/ወይም አለሩካቤ ሥጋ)፡፡ ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ፡፡…. የጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 7፤ 7-9

ይህ የጳውሎስ መልእክት የሚጠቁመን ምርጫ ያለን መሆናችንን ነው፡፡ ዘርን ከመተካት መለኮታዊ ትዛዝና ተፈጥሯዊ የተዋስቦ ህግ አንጻር ተገቢነቱ እጅግም ነው ብዬ በበኩሌ ባምንም አለማግባት በመሠረቱ ጥሩ ነገር ነው፤ ማግባትም ጥሩ ነገር ነው፤ በምናብም ይሁን በእውን በአንዴ ሁለቱን መሆን ግን ፈጽሞ አይቻልም፡፡ መሆንና አለመሆን በአንድ ጊዜ አንድ ቦታ ላይ የሚገኙበት ተጠየቃዊ ኹነት የለምና፡፡

እንዲያውም እሳትን በጉያ ይዞ እየነደዱ ከመኖር ይልቅ በህጉ መሠረት አንዲት አግብቶ እየተቃጠሉ ማነው እየወለዱና እየከበዱ መኖር የተሻለ አማራጭ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት ሰዎች የማይችሉትን ቀምበር ለመሸከም የሚንደፋደፉትና ቅሌት ውስጥ የሚዘፈቁት ለምንድን ነው? ብለን መጠየቅ ደግሞ ይኖርብናል፡፡

ለእህል ውኃ ነው? ለክብር ነው? ለዝና ነው? ለየትኛው ክብርና ዝና? ክህነትን ያህል ትልቅ ማዕረግ፣ ጵጵስናን ያህል አቢይ መለኮታዊ ሥልጣን አፈር ድሜ አስግጦ ራስን ለማዋረድ ይህን ያህል ርቀት መጓዝ ለምን አስፈለገ? አርሶና ቆፍሮ መብላት፣ ነግዶና ተቀጥሮ መሥራት እየተቻለ በእግዚአብሔር መቀለድ በምንም ሚዛን ቢለካ ተገቢ አይደለም፡፡ ክህደት ነው? ልብንና ኩላሊትን የሚመረምር አምላክ ነውሬን አያውቅብኝም ነው? ምንም አያደርገኝም ነው? ችግሩ ምን ይሆን? በየጥምጣሙ፣ በየጥንግ ድርቡ፣ በየካባውና ቀሚሱ ውስጥ ያለው ነገር ቢፈተሽ የእግዜርን ትግስት በእጅጉ እንድናደንቅ ያደርገናል፡፡ አዎ፣ ሞት ሲዘገይ የቀረ ይመስላል፤ ጥቂት እንፈላሰፍና – ምፅዓት የሞት ታላቅ ወንድም እንቅልፍ ደግሞ የሞት ታናሽ ወንድም ናቸው፡፡

ሁሉም ግን ጊዜያቸውን ጠብቀው መምጣታቸው አይቀርም፡፡ የማይመጡ እየመሰለን ግን ተሳስተን እናሳስታለን፡፡ ወዮ ለካህናት! ወዮ ለእረኞች! በጳውሎሳዊ ቃል “ወዮ! ቆሞ ያለ ለሚመስለው ዕቡይና ዝንጉ – የተቀመጠስ እንዴውኑ ተወዝፏል”፡፡

በኛው ቤተ ክርስቲያን እንዲህ የጨከንኩ መሰልኩ እንጂ በካቶሊክም ሆነ በእስልምናውና በአይሁዳውያኑ ረገድም አጮልቀን ብናይ እውነቱ ከዚህ የተለዩ አይደለም፡፡

እኛ ጋ እነልደቱ አያሌውና እነ"አቡነ" እንጦስ ጽላት እየሸጡ እግዜርን በሰው ፊት "ሲያቀሉ"ና "ሲያዋርዱ" በአውሮፓ ደግሞ የገነት መግቢያ ካርድ(Indulgence Card?) ለምዕመናን እየሸጡ የሚከብሩና በፈጣሪ የሚቀልዱ ዚቀኛ ካህናትና ጳጳሳት ነበሩ – በመካከለኛው ዘመን አካባቢ፡፡

እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች አሁን አሁን ሁሉን ነገር እርግፍ አድርገው – ጌታን በትክክለኛው መንገድ ማገልገሉን ሆን ብለው ትተውት – ወንዶችና ሴቶች ሕጻናትን በማስገደድና በከረሜላ በማታለል መድፈር፣ እርስ በርስ በተመሳሳይ ፆታ የወሲብ ግንኙነት ተጠምደው ዲያብሎስን በሙሉ ልብ ማገልገል፣ በዘረፋና በማጭበርበር በሚያገኙት ገንዘብ የግል ሀብትን ማከማቸት… ዋና ሥራቸው በማድረግ በሥጋ ገበያ ጠፍተዋል – (አንድ የኢቫንጀሊካን ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ በጀርመን ሀገር የ 42 ሚሊዮን ዶላር ቤተ መንግሥት መሰል መኖሪያ እንዳሠራና ከኃላፊነቱ እንደተባረረም ቀደም ሲል ሰምቻለሁ – ሁሉም ያው ቢሆኑም ለይምሰል ብለው በወቅቱ እርምጃ ወስደውበታል)፡፡ አብዛኛው ምዕመን በነዚህ ሰዎች ተስፋ በመቁረጥና በሕይወት ጨለምተኝነት በመሸነፍ ቤተ ክርስቲያንንና ሃይማኖትን እየተወላቸው መውጣቱን ተያይዞታል፡፡

ይህ አካሄድ ደግሞ እየገነነ ለመጣው ለሌላኛው ሰይጣናዊ ክንፍ ለአክራሪ እስልምና መስፋፋት የበኩሉን ድርሻ እያበረከተ ነው – ዛሬስ የጤና ያድርግልኝ፡፡ ምን ነካኘ ግን? ከስንቱ ጋር ነው "የምናጀሰው" በል?…
አዎ፣ እንግዲህ ያለንበት ሁኔታ በሁለትና ሦስት ዐረፍተ ነገሮች ሲገለጽ ይህን ይመስላል፡፡ በአንድ ወይ በሌላ መልክ ሁላችን ጠፍተናል፡፡ ከጠፋነው ይልቅ ደግሞ ልንጠፋ ያሰፈሰፍነው እንበልጣለን፡፡

ዓለማችንን ከያቅጣጫው ስንታዘባት አእምሮ ጠፍቶ ሕገ አራዊት የሚሉት ነገር ነግሦ እናያለን፡፡ ዓለማችን የአንድ ዓመትን ወንድ ሕጻን በቡድን የሚደፍሩ የታሊባን አክራሪ ሙስሊሞች፣ የሦስት ዓመት ወንድ ሕጻንን በቡድን የሚደፍሩና በመጨረሻ የሚገድሉ አክራሪ ሙስሊሞች በገፍ እየቀፈቀፈች ወደ ጨለማው ንጉሥ ግዛት ማስገባቷን ስንረዳ ምን ያህል እንደቆሸሸችና የመጽኛ ጊዜዋም ምን ያህል እንደቀረበ እንገነዘባለን፡፡ (ለነዚህ ወሬዎች ይህን ቦታ ፈልገው ያንብበቡ – walidshoebat.com) ብዙ ጉድ እየፈላና እየተንተከተከ ነው፡፡ አይቀርልንም፡፡ እናም እንዘጋጅ፡፡
ዘረኝነትም አንዱ ከፈጣሪ የሚለየን መጥፎ ወረርሽኝ ነው፡፡ ለአንድ የሰው ልጅ ዘር ወደ ዓለም መጥቶ የተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ ትግሬ ወይ አማራ ወይም ኦሮሞ አልነበረም፡፡ ምንም እንኳን አንዱን የሰው ዘር መምሰል ስለነበረበት ክርስቶስ ኢየሱስ ከይሁዳዎች ዘር ቢፈጠርም ዓላማውና ግብሩ ግን ለመላው የሰው ዘር ነው፡፡

እነ መለስና አባቶቻቸው እነጳውሎስ ግን ቤተ ክርስቲያንን ለሰይጣን ማደሪያ በማድረግ ከቀደሙት አባቶች ባሱና ሕዝብን በቀበሮና በተኩላ ያስጨርሱት ገቡ፡፡ ሁሉም ዋጋቸውን ሊያገኙ ጦርነቱ መጀመሩ ተስፋ ይሆነናል እንጂ በዚህ በያዙት መንገድ ብዙ ዓመታትን መቀጠላቸው ግድ ቢሆን ኖሮ በእጅጉ እንናደድ ነበር፡፡ "ለሁለት ጌቶች መገዛት አይቻልም" የሚለቀውን የፈጣሪ ህግ አፍርሰው ከሁለት በላይ ለሆኑ ህግጋት አፈነደሱ – ለዘር፣ ለንዋይና ለሃይማኖታዊ ህፀፅ፡፡

የምድር ነገር ምድራዊ ነውና እንደጥላ ያልፋል፤ እንደጤዛም ይረግፋል፡፡ የሚቀረው ግን በቀላሉ የማይሽረው የታሪክ ጠበሳውና ስብራቱ ነው፡፡ ለወያኔ ዲያብሎስና ለእግዜር በአንዴ መገዛት እንደማይቻል ጎሊናን ትንሽ ከፊት አድርጎ ማየት ነው፤ እምብርት ላልተበጀለት ላስቲክ ሆድ ሲባል ሀገርንና ህዝብን ከዶ ለአንድ ዘረኛ ቡድን ማደግደግ ቀን ሲያልፍ ለሀፍረትና ለትልቅ ውርደት እንደሚዳርግ ማወቅ በተገባ ነበር – ጭንቅላት የለም እንጂ ቢኖር ኖሮ፡፡

ለማንኛውም ዛሬ እንዲህ ነው፤ ነገ ግን በርግጠንነት ይለያል፡፡ ተስፋ ሲሞት ሰው ይሞታል፡፡ ተስፋ ካለ ሰው አለ – እኛም አለን፡፡ ከሚተርፉት ከመደበን ጦርነቱ ሲያልቅ እንገናኝ ይሆናል፡፡ ሰላም፡፡

ቀጣዩን ነገር ከፈለጋችሁ አንብቡት – ልተረጉመው ብዬ አስቀመጥኩት – ግን ደከመኝና ተውኩት፡፡

Deviancy never resides in one desire, like murder; deviancy resonates in all desires, it becomes a part of one's whole person. Deranged and disturbing lusts for blood resonates in one's sexual urges, and these are always aberrant and debased. It all comes down to one's religious beliefs. All deviancy originates from a disordered view of God. If one's soul is loving, then that soul will treat his or her spouse with love. But if one's soul is darkened by evil, then that person will not care for love, harmony, compassion, no, not even the natural order. Chaos is embraced, order is mutilated, and the entire divinely created system of nature is warred against. (source: walidshoebat.com)